# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!






- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ Yeec.org App ጭነዋል?
- ⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?

ሽማግሌዎችን ለማግኘት፡-
773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)
773-507-0147 (ወ/ም ጸደቀ)
630-677-0293 (ዶ/ር ተረፈ)
773-910-0486 (እ/ት ሰናይት)
773-556-5345 (ወ/ም ረድኤቱ)

**<u>መደበኛ ፕሮግራሞች</u>**
እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | | Chicago Yemsrach Evangelical Church |
|---|---|---|

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2:10




**"በጌታ ፊት ራሳችሁን አዋርዱ ከፍ ከፍም ያደርጋችኋል።"**
(ያዕ. 4:10)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

መደበኛ ፕሮግራሞች
እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

**September 08, 2019** | **ነሐሴ 26 ፤ 2011 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

ጸሎት ............................ ወንድም ጌቱ ጳውሎስ

አምልኮ.......................... የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን

ፕሮግራም መሪ ............. ወንድም ረድኤቱ ካሳ

ቃል ................................ ወንድም ሲሳይ መሸሻ

ማጠቃለያ ...................... ፕሮግራም መሪ

## የሳምንቱ ጥቅስ

"እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ ዲያብሎስን ግን
ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል፤
ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል።
እናንተ ኃጢአተኞች፥ እጆቻችሁን አንጹ፤ ሁለት
አሳብም ያላችሁ እናንተ፥ ልባችሁን አጥሩ።"
(ያዕ. 4:7-8)

| የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች | | |
|---|---|---|
| መሪ | ቀን | አድራሻ |
| ወ/ም አያሌው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7319 N Oakley Ave, Chicago, IL 60645 |
| ወ/ም ጌቱ ጳውሎስ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሃሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| | | |

# መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም መስፍን ባፋ

## መጠበቅና መጠባበቅ

ሰው ተስፋ ያደረገውን ማንኛውንም ነገር የመጠበቅ ዝንባሌ አለው።መጠበቅ በራሱ ክፋት የለውም።በሌላ መልኩ በእጅ ያለውን፣የተያዘውን መጠበቅ ወይንም መንከባከብም ተገቢ ነው። ቀጠሮ የተቆረጠለትን፤ቀንና ሰአት የተወሰነለትን ነገር መጠበቅም መጥፎም አይደለም።ነገር ግን በመጠበቅ ውስጥ መዘግየት አለ።የሁኔታዎች መዘግየት ደግሞ ዝለት፤ዝንጉንትን፤ቁጣንና ተስፋ መቁረጥን ይወለዳል።መጠባብቅ ውስጥ ግን መታደስ ፤መዘጋጀት፤ ተስፈኛንትና መበርታት አሉት። እነዚህም የመጠባበቅ መለያ ባሂሪያቶቹ ናቸው።

በሉቃስ ወንጌል መዕራፍ 15:25-32 ጠፍቶ ስለተግኘው ልጅ ሳይሆን ለገዛ አባቱ እንደ ተቀጣሪ ዘመኑን በሙሉ ያገለገል የታላቅ ልጅ ታሪክ እናያለን።ይህ ታላቅ ልጅ አባቱን ሲያገለግል የከርመው አንድ ቀን ድርሻውን ከአባቱ ለመቀበል በመጠበቅ ስሌት ነበር። የዚህ ወንድም መጠበቅ በደስታ ሰአት እንዲቆጣ እንዳደረገውና አባቱንም ጠርቶ እስከ ዛሬ ሳገለግልህ ከባልንጀሮቼ ጋር እንድደሰት የፍየል ግልገል እንኳን አልሰጠሄኝም ብሎ አባቱ ያልግመተውን ዱብ እንዳድረግ እናያለን ።ልብ ስንል አባቱ ለልጁ ያሰበለት ግን እጅግ ከፍ ያለና ከተራ የፍይል ግልገል እጅግ የላቀ መሆኑንም እንገነዘባለን(ሉቃስ 15:31-32)።

የአስሩን ልጃገረዶች ታሪክ በማቴዎስ ወንጌል 25፤1 13 ደግሞ ስንመለከት አምስቱ ይጠብቁ አምስቱ ድግሞ ይጠባበቁ እንደነበረ እንርዳለን።ምክንያትም "አምስቶቹ ልጃገረዶችህ እየተጠባብቁ ስለነበረ መጠባበቂያ ዘይት በማሰሮ ይዘው በንቃት ይጠባቁ ነበር። 'ቀኒቱና ስ አቲቱን አታውቁምና ንቁ።"(ማቴዎስ 25:13)

ነገር ግን የሙሽራው የመምጣቱ ደውል ሲመታ ሲጠባበቁ የነበሩት መብራታቸውም ተርኩሰው ከሙሽራው ጋር ወደ ሰርጉ ቦታ እንደገቡና አብረውም እንደታደሙ እናያለን።እንግዲህ መሽራው እንድሚመጣ እንጂ መቼ እንደሚመጣ አልተነገራቸውም። ከክፍሉ እንድምንረዳው መዘግየቱ ራሱ የታውቀው እኩለ ሌሊት በማለፉ ነበር።እነሱ ግን ዝግጁ ነበሩ።

ልብ እንበል ቀን ያልተቆረጠለትን ተስፋ የምናድርገውንም ነገር መጠበቅ አንችልም።ምክንያቱም የሚጠብቅ ይዘነጋል፤ይዝላል፤ተስፋ ይቆርጣል ከዚያም ሲያልፍ አይዘጋጅም። እነዛ አስተዋዮቹ ልጃግርዶች ግን መጠባበቂያ ከመያዛችውም ባሻግር የባሰ ቢመጣ ብለው ተጨማሪ ዘይት የሚገዛበትን ቦታ ሁል እንድሚያውቁ እረዳለሁ።

እኛ አማኞች ክርስቶስ ዳግም እንደሚመጣ አጥብቀን እናውቃልን። የመምጣትንም ምልክቶች ከቅዱስ ቃሉ ተምረናል።ቀኑና ሰአቱን ስለማናውቅ እንድንዘጋጅ ነው ትዕዛዝ የተቀበልነው። ስለዚህ መጠበቅ ሳይሆን መጠባበቅ ነው ያለብን።ስንጠባብቅ ቀንዳችን ከፍ ከፍ ይላል።መጠባብቅ ተስፋ አለውና የቀናትና የሰአታት ሉጋም አይገድቡትም። ሁሌም በአዲስ ሃይል አዲስ እየሆንን እንጓዛለን።

መጽሐፍ ቅዱሳችንም በኢሳያስ 40፡31 "እግዚአብሄርን በመተማምን የሚጠባበቁ ግን ኃይላቸውን ያድሳሉ፤እንደንስር በክንፍ ይወጣሉ ይሮጣሉ፣አይታክቱም ይሄዳሉ፤አይደክሙም።" ይልናል። ተስፋ የምናደርግም እየሱስ በእርግጥም ይመጣል ነገር ግን ቀንና ሰአቱን ልናውቅ አልተፈቀደልንምና ሃይላችን እንዲታደስ፤በክንፍ እንድንወጣ እንዳንደከም ከመጠብቅ ህይወት ወደ መጠባብቅ ህይወት በጋር እንሽጋገር።እግዚአብሄርም ይርዳናል። አሜን።